## ፓኖራማ ቁጥር 100

## የትዝብት አድማስ

ኅዳር 26 ቀን 2003 ዓም

## ለለውጥ ያልተዘጋጀ ሕዝብ የለውጡን ድል ( ፍሬ ) ይነጠቃል

የዚህ ሐተታ ርዕስ ፥ በአለፉት አርባ ዓመታት በሀገራችን የተከሰተውን የፖለቲካ ሀቅ ያንፀባርቃል ብለን እንገምታለን ። በዚህ በተጠቀሰው ዘመን ሦስት ሥርዓቶች ተፈራርቀዋል ።ሦስቱም በተለያዩ ጽንፎች ረድፍ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው ።አንዱ ከሌላው ጋር በይዘት፥በቅርፅም ሆነ በባኅርይ ጽንፈኞችና ተፃራሪዎች ናቸው። መነሻና መድረሻቸው፥ ተልዕኳቸውና ግባቸው ፥ ድርጊታቸውና ዕምነታቸው/ ርዕዮታቸው የተለያየ ሆኖ ፥ ይህ ልዩነታቸው ግን አምባገነን በመሆናቸው ብቻ በአንድ ሚዛን እንዲመዘኑ ያደርጋቸዋል ። ሁሉም የአምባገነን ሥርዓት አራማጆች በመሆናቸው ብቻ ደግሞ ሁሉንም በአንድ ሰፌድ አስቀምጦ ማበጠር ትክክል ነው ብሎ ማለት የሚቻል አይሆንም ።

የአፄውንና የደርግን ሥርዓቶች፥ በዘር ላይ ከተማከለው የወያኔ ሥርዓት ጋር ለመፈረጅ የማያስችል በቂ ምክንያት እንዳለ ግን እንገነዘባለን ። ምንም እንኳ ሁለቱም ሥርዓቶች ያፈጠጡ ያገጠጡ አምባገነኖች እንደነበሩ ባይካድም፥ሕዘብን መበደላቸውና መጨቆናቸው ሀቅ ቢሆንም ፤ ይሁነኝ ብለው ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት እንዲከፋፈል አላደረጉም ። በአምባገነን ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ሕገመንግሥት ቢጽፉም እንኳ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተለያይቶ እንዲገነጣጠል የሚያስገድደውን አንቀጽ በጻፉት ህገ መንግሥታቸው ውስጥ አላሰፈሩም ።ይህ ሀቅ ብቻ ከወያኔ የተለዩ እንዲያደርጋቸው በቂ ምክንያት ይሆናል ። ሌላው ሁሉ እንዳለ ሆኖ ፥ በአምባገነን ሥርዓት የሚገዙትን ሕዝብም ሆነ ሀገር በወያኔ ደረጃ በባዕድ አላስደፈሩም ። የሀገርንና የሕዝብን ታሪክ አላዋረዱም። ይህ ፥ የወያኔ ብቸኛና ዋነኛ ተልዕኮ ነው ።

ተራማጅ ኃይሎች <u>መሬት ለአራሹ</u> ! ብለው ተሰው እንጅ፥ የኢትዮጵያ ለም መሬት ለውጭ ባለሀብቶች ይሸጥ-ይለወጥ ብለው አልታገሉም። ይህ አሳፋሪ የክኅደት ተግባር በሁለቱም አምባገነን ሥርዓቶች አልተፈፀመም ። ቢያንስ፥ ለሀገራቸው የነበራቸው ቀናዒነት ይህንን እንዳያደርጉ አግዷቸው እንደነበር መካድ አይቻልም ። ይህ አስነዋሪ የክኅደት ድርጊት

እየተፈፀመ ያለው ዛሬ በወያኔ ከሀዲ ቡድን ዘመን ነው ። በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ስም የተደራጀው ይህ ከሃዲ ዘረኛ ቡደን የሚፈጽመውን ሀገራዊ ወንጀል፥ የትግራይ ሕዝብ ይደግፈዋል ፥ይስማማበታል ማለት ግን አይደለም ። ይህን ሀቅ ማስመዝገባችን ወያኔን የተቃወመ ሁሉ ፀረ ትግሬ አቋም አለው የሚለውን የወያኔን የዘር ፖለቲካ ቁማር ጨዋታ ፍሬ -ከርስኪ እንደሚያርገው ስለምናውቅ ነው ።

የዛሬይቱ ዓለማችን አሁን ካለችበት ደረጃ ልትደርስ የቻለችው፥ ያልተቋረጠና ያልተገደበ ለውጥ እያደረገች ለመሆኑ ብዙ መስመር ሊጻፍለት የሚያስፈለግ አይደለም ። ሀገራችን ኢትዮጵያም የዓለም ኅብረተሰብ አካል በመሆኗ በዚህ የለውጥ አውታር ዙሪያ የምትሽከረከር ነች ። በመሆኑም ፥ የለውጡ ወላፈን በቀጥታም ይሁን በተዘዋወሪ ያገኛታል ።የሀገራችን ሕዝብም እንደዚሁ በታሪኩ የአምባገነኖች ጭቆና ሰለባ በመሆኑ በግድ የተሻለ ዕድል ለማምጣት ሲል ለውጥ እንደሚያስፈለግው በተደጋጋሚ ያሳየው ክስተት ነው ። ከጭቆና ለመላቀቅ ሲል በሚያደረግው የለውጥ እንቅስቀሴ አይከፍሉ መሥዋዕት እንደከፈለና አሁንም በመክፈል ላይ እንዳለ፥ ከእርሱ በቀር ማንም የሚያውቅለት አልነበረም። አሁንም ማንም የለ ። ለተሻለ አስተዳደርና የዴሞክራሲ ሥርዓት፥ ለፍትኀ-ርትዕ፥ለልማት ዕድገትና ብልፅግና ሲባል ከየካቲት 1966 ዓ ም ጀምሮ ለውጥ ለማየት ቢፈልግም ፥ የለውጡን ውጤት ለማግኘት የነበረው የጋለ ፍላጎትና ለውጡን ለማስተናደገድና በሌሎችም እንዳይነጠቅ ለማድረግ የነበረው መሰናዶ ተመጣጣኝ ስለአልነበረ ፥ በጥቂት ሥልጣን ጥመኞች ተነጠቀ ። ይህ ክስተት ባለፉት አርባ ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሁለት ጊዜ ተፈጽሞበታል ።

የመጀመሪያው የየካቲት 66 ሕዝባዊ ዐብዮት ድል በምርጥ መኮንኖች ተነጠቀ ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ ፥ ባኅል ፥ሥነምግባር ፥የቆየውን ችግር፥ የወደፊቱንም ተስፋና ራዕይ በትክክል ባልገባቸው ጥቂት መኮንኖች ተዘረፈ ። አስራ ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ የደም እምባ አስለቀሰው ፥ ይህ ነው የማይባል ብሔራዊ ወንጀል ፈጽመው ጠፉ ። የተከሉት አምባገነናዊ መዋቅርም ተንኮታኩቶ ቀረ ። ሀገሪቱንም በላኢ-ሰብ፥ በላኢ-ሀገር ለሆነ አምባገነን ዘረኛ ቡድን አስረክበዋት ሄዱ ። የአስራ ሰባቱን ዓመተ-ፍዳና ምዕኣት ሁኔታ መዘርዘር የዚህ ጽሁፍ ወቅታዊና አጣዳፊ ተልዕኮ ስለአልሆነ ፥ትኩረታችን በእሱ ላይ አይሆንም ። አንድ ዐብይ የሆነ ሀገራዊ ጉዳይ ግን ማስመዝገብ እንፈልጋለን ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ የደርግን አምባገነን ሥርዓት ለመለወጥ ባደረገው መሪራ ትግል ፥ ተዘርዝሮ የማይፈፀም መስዋዕት ከፍሏል። ዕልፍ ኣዕላፍ ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል ።አካላቸው የጎደለ፥ እዕምሮቸው፥ የተሰናከለ፥ ሀብት ንብረታቸው የወደመ ዜጎችን ቁጥር ለመመዝገብ ራሱን የቻለ ተቋም ስለሚያስፈልግ ይህንን ተግባር ለማከናወን ዛሬ የሚቻል አይደለም ።

የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር ሲል በየጠረፉ ደሙን ያፈሰሰው፥ አፅሙን የከሰከሰው የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የከፈለው መስዋዕት መና ሆኖ ቀርቷል ባይባልም ፥ ያ ሁሉ መሥዋዕት ተከፍሎ ፥ አሁን ሀገሪቱ ያለችበትን አሳዛኝ ሁኔታ ሲመለከት ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀዘኑን አጥፍ ድርብርብ አድርጎበታል ። ያስራ ሰባቱ መራር ትግሉ ፥ የከፈለውም እጅግ ከባድ መሥዋዕት፥ የጠበቀውን የመሥዋዕት ውጤትና ለውጥ ሳያስገኝ እንዴት ቀረ ? እያለ የሚብተከተከው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስተማማመኝ መልኩ በቂ መልስ ሊያገኝ የሚችለው፥ በትግል የከፈለውን የመሥዋዕት ውጤት ፥ በጥቂት የሥልጣን ጥመኞች እንዳይነጠቅ የሚያስችለውን ኃይል ሲያገኝ ብቻ ነው ። ለለውጥ የሚደረግ ትግልና የለውጥን ፍሬ ለማግኘት የሚደረገው ሂደት አስተማማኝና ተመጣጣኝ ባለመሆኑ፥ በስድሳ ስድስት ዓ ም የሆነው ፀረ ሕዝብ ውንብድና እንደገና በሰማኒያ አንድ ዓ ም መልኩን ለውጦ ተደገመ ።

ጳግመኛው ፦ ደርግን ለመጣል በተደረገው የአስራ ሰባት ዓመታት መራራ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ከባድ ብሔራዊ መሥዋዕት ቢከፍልም፥ አሁንም እንደ ትላንቱ የለውጥ ፍላጎቱና የለውጡን ፍሬ ለማግኘት የተደረገው ዝግጅት ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ፥ የትግሉን ድል በጥቂት ዘረኞች ቡድን ተነጠቀ ። የታሪክ ዕንቆቅልሹ ግን ፥ ወታደራዊው ደርግ፥ " የታሪክ ተልዕኮ " አለብኝ በሚል መፈክር የብሔራዊ ራዕይን እያቀነቀነ ፥ ብሔራዊ ጥፋትን አጥፍቶ ሲጠፋ፥ ወያኔዎቹ በበኩላቸው የአንድ ጎጥ ጥቅምና ፍላጎት አቀንቃኝ በመሆን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላቶች መሆናቸው ነው ። ይህ ዕውነታ ፥ በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ያለችውን ሀገራችንን ፥ የታሪክ ዕንቆቅልሽና የጠላቶቿ ምፀት ሰለባ እንድትሆን አድርጓታል ።ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ **" የተናቀ ሀገር በአህያ ይወረራል "** የሚል የምፀት ተረብ እየተተረተባት ነው ። የሀገሪቱ ብሔራዊ ችግር ፥ በምፀት ውርደት ዙሪያ የሚሽከረከር ሳይሆን ፥ ከውርደቱ፥ ከጥቃቱና ከምፀቱ ባሻገር የተመለከተ መፍተሔን የሚጠይቅ ነው ። ያስራ ሰባት ዓመታት መራራ ትግል ያመጣው ለውጥ ደርግን አስወግዶ ወያኔን የተካ ከሆነ፥ ዛሬ ወያኔን ለማስወገድ የሚደረገው ትግል ፥ የነገን የለውጥ ድል የሚያረጋግጥ መሆኑ ቀርቶ፥ የሕዝቡን ድል ለሌላ ነጣቂ አውሬ የሚያስረክብ እንዳይሆን በአጽንዖት ሊታሰብበት ይገባል። **" ካለፈ ታሪክ የማይማር ሕዝብ ራሱን እየረገመ ይኖራል "** እንዳንባል ፥ ወያኔን አስወግዶ ለሚተካው ሥርዓተ- መንግሥት ዛሬውኑ በቂ ዝግጅት መደረግ እናዳለበት ሁሉም ሊያስብበት ይገደዳል ። **የዋርካ ፍሬ ማፍራት ፥ የጠቀመው አዕዋፍን እንጅ፥ ለዋርካው ዛፍ አልበጀውም** ፥እንደሚባለው፥ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና አንድነት እየታገለ የተሰዋው አይበገሬው ትውልድ ዓላማና ራዕይ የት አለ? እምን ደረሰ ? ብሎ መጠየቅ፥ የነገዋን ኢትዮጵያ ብሩኅ ተስፋ ለሚፈልግ ዜጋ ሁሉ፥ እንደ እግር እሳት የሚያንገበግበው ዐውደ-ኃሳብ ነው ።

*በወያኔ ዘረኛ ቡድን ስር ስለምትማቅቀው ሀገራችን ብዙ ስለተባለ ፥በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ልናክልበት የሚኖር አዲስ ነገር አይኖርም ። ከዚህም በቀር ዘለዓለም ስለችግር እያወሩ መቃጠል፥ ቅንጣት ያህል መፍተሄ አያመጣም ባዮች ነን ። ይልቅስ ይህ ሰማኒያ ሚሊዮን የሀገራችን ሕዝብ ለአራተኛ ነጣቂ ጠላት እንዳይጋለጥ መሠረታዊና ዘላቂ መፍትሔ መፈለግ ወሳኝ መሆኑን ማመን ይገባል ። ይህንን ዕምነት ተግባራዊ ለማድረግ የመጀመሪያው ርምጃ በኢትዮጵያ ብሔራዊና ዘላቂ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ፥ የብሔራዊ አርነት ትግል መጀመር ተመሳሳይ ስህተትና ጥቃት እንዳይመጣ ዋስትና ይሆናል ።*

" **የጦርነት ጥቃት እንዳያገኝህ ከፈለግህ፥ በሰላም ጊዜ ለጦርነት ተዘጋጅተህ ጠብቅ** "
የሚለው መርኅ ለለውጥ ፈላጊ ኅብረተሰብም ጭምር ዓይነተኛ መርኅ ሆኖ ያገለግላል ብለን እናምናለን ። በመሆኑም ፥ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ትግል፥ የመጨረሻ ድሉ፥ አዲስ ባቀበቀበ አምባገነን እንዳይነጠቅ ፥አስቀድሞ ብልሀት ሊዘጋጅለት ይገባል። ከአለፉት አርባ ዓመታት ጀምሮ የሚካሄደው ሕዝባዊ አመፅ አሁንም እንደገና ለሌላ አራተኛ አምባገነን ሥርዓት እንዳይጋለጥ ሁሉም በያለበት በብርቱ እንዲያስብበት አደራ እንላለን ። ለተሻለ ለውጥ የሚታገል ሁሉ የሚመጣውን ለውጥ ለመረከብ እስካልተዘጋጀ ድረስ፥ አምባገነኖች ሀገሪቱን አዘጋጅተውለት አይሄዱም ። ከጠፉም በኋላ ሲገዙት የነበረውን ሕዝብና ሲበዘብዟት የቆይዋትን ሀገር በታትነውና አጠፋፍተው የሚሄዱ ለመሆናቸው ባለፉት አርባ ዓመታት በገሀድ የታየ ክስተት ነው ።

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ! ውሃ ውሃ ሀጂ ፥ አለቱ ግን ቀሪ ነው እንደሚባለው፥ ሀገርህ ኢትዮጵያና አንተ/አንቺ ብቻ ቀሪዎች ስለሆናችሁ፥ አንድነትንና ኃይልን አጠናክሮ ለአራተኛ ጊዜ የለውጥን ድል ላለመነጠቅ ነቅቶ መጠበቅ ያስፈልጋል። ወያኔ በኢትዮጵያ የለውጥ አመፅ ጎርፍ ተጠራርጎ እንደሚጠፋ ቅንጣት ያህል ብዥታ ሊኖር አይገባም።*